# አንድ ሕዝብ ነን ወይስ አይደለንም ።

"እኛ ኢትዮጵያውያን አንድ ሕዝብ ነን" ከሚሉት አንዱ ነኝ ። አንድ ከሆንን ለምን እንጋጫለን? "በልዩነት አንድነት" የሚል አነጋገርም አለን ። በልዩነት አንድነት ይቻላል ወይ? ልዩነታችንን ጠብቆ አንድ የሚያደርገን ምንድን ነው? ያንን አንድ የሚያደርገንን ሁላችንም ካልተቀበልነው ፥ አንድነትን ምንም ያህል ብንሰብከው እንደማግኔት አሉታ ተራርቀን እንኖራለን እንጂ አንቀራረብም ።

ባልና ሚስት የተለያዩ ናቸው ። እሱ ወንድ ነው ፤ እሱዋ ሴት ናት ። "አንድ ነን" ሊሉ የሚችሉት ትዳር ለመመሥረት ስለተስማሙ ነው ። የተለያዩ ሆነው ሳለ ፥ አንድ የሚያደርጋቸው ሁለቱም የተቀበሉት ምክንያት አገኙ ማለት ነው ። ክርስቲያኖች የተለያዩ ሰዎች (ከተለያዩ ነገዶች) ሊሆኑ ይችላሉ ። "አንድ ነን ሊሉ" የሚችሉት ሁሉም የተቀበሉት አንድ ዓይነት የአምልኮ ሥርዓት ቢኖራቸው ነው ። አንድ ዓይነት ያልሆኑ ሕዝቦችን ሃይማኖት አንድ አደረጋቸው ። ቋንቋም አንድ ያልሆኑ ሕዝቦችን አንድ የማድረግ ኀይል አለው ። ኦሮሞችን አንድ ያደረጋቸው ቋንቋ ነው ። አማሮችንም አንድ ያደረጋቸው ቋንቋ ነው ። ኀጥና ዘርም አንድ ያደርጋሉ ። አንድ የሚያደርጉ ነገሮች ሁሉ ከሌላው ይለያሉ ። "እኛ አንድ ነን" ማለት "ከሌላው የተለየን ነን" ነን ማለት ነው ።

አንድ ምክንያት አንድ ያደረጋቸውን ሕዝቦች ፥ ሌላው ምክንያት መጥቶ ይበትናቸዋል ፤ የተለያዩ ሕዝቦች ያደርጋቸዋል ። ቋንቋ አንድ ያደረጋቸውን ሃይማኖት የተለያዩ ያደርጋቸዋል ። ባህል አንድ ያደረጋቸውን ሰዎች የትውልድ ቦታ የተለያዩ ያደርጋቸዋ ። በዚህ ምክንያት እኮ ነው ፥ "ተጋብተናል ፥ ተዋልደናል ፥ ደማችን አንድ ነው" የምንለው እውነታ ሁሉ ልብ ለመማረክ አቅም ያነሰው ። በዚያ ላይ መናናቅ አለ ። የጎሳን ስም እየጠራን የስድብ ቃል የምናደርገው አለን ። ከኦሮሞች ጋር በነበርኩበት የልጅነት ጊዜ "ሲዳምቲቲ እነና" እየተባልኩ ነው ያደግሁት ። አማሮቹም ስድብ አላቸው ። ዋናው እዚያም ቤት እሳት መኖሩን አለመዘንጋት ነው ።

ኢትዮጵያዊ ሥነ ጽሑፍ የዳበረው ፥ ኢትዮጵያዊ መንግሥት የተቋቋመው ኦሮሞዎች ማህል ኢትዮጵያን ከመውረሳቸው በፊት ከወደሰሜን በኩል ስለሆነ ፥ ይህ ታሪክም እንደ ሃይማኖትና እንደ ቋንቋ ፥ በሰሜኖች (ትግራይ-አማራ) እና በኦሮሞዎች መካከል ከሁሉም የከፋ ልዩነት ፈጥሯል ። የኦሮሞ ፖሊቲከኞች ፥ "ሥነ ጽሑፉም መንግሥቱም ምናችን ናቸው?" ሲሉ ይሰማሉ ። ያለፈ ታሪክንና ጊዜን ጠርቶ በፈለጉት መንገድ ማስኬድ አይቻልም ። ከሰዓት በኋላ የደረሱ ሁሉ ፥ ኢትዮጵያን ገናና ያደረጋትን ከሰዓት በፊት የተፈጸውን ማክበር ውዴታችንም ግዴታችንም ነው ። ግን እኮ ኦሮሞዎች ወደማህል ኢትዮጵያ ከገቡ ወዲህ በሁለቱም ሥርዓቶች (በመጻፍም ፥ መንግሥቱን በማካሄድም) እኩል እንደተሳተፉ ያፈጠጡ ማስረጃዎች አሉ ። ሥራ ማስኬጃው (ቋንቋው) አልተቀየረም እንጂ ሠራተኞቹ ተለውጠዋል ። አስተዋፅኦው የሁሉም ሆኗል ።

"አንድ ሕዝብ ነን" እንዳንል ፥ አንድ ሕዝብ እንዳይደለን የሚከለክሉን ምክንያቶች ከላይ ተዘርዝረዋል ። አዲሶቹ መሪዎቻችን ቢቸግራቸው ፥ "ብሔር ፥ ብሔረ ሰብ ፥ ሕዝቦች ሆይ" እያሉ ይጠሩናል ።

እልዩነታችን ላይ ስለሚያተኩር ፥ ጥሩ መፍትሔ አይደለም ። “ብሔር ፥ ብሔረ ሰብ ፥ ሕዝቦች” ሲባል ፥ የትኛው መጠሪያ ነው የትኛውን ኢትዮጵያዊ የሚያመለክተው? “ብሔር” ሲል ፥ “አቤት” የሚል ፥ “ብሔረ ሰብ” ሲል ፥ “ብሔረ ሰብ” እስከሚባል ጠብቆ ፥ “ሕዝቦች” ሳይባል ቀደም ብሎ ፥ “አቤት የሚል” ፥ “ሕዝቦች” እስኪል ሲል ቆይቶ “ሕዝቦች” ሲል “አቤት” የሚል ኢትዮጵያዊ ማነው? በሌላ አነጋገር ፥ “መጠሪያየ ይኼኛው ነው” የምንለው የትኛውን ነው? “አቤት” ለማለት ተራችን መቼ ነው-- “ብሔር” ሲባል ፥ ወይስ “ብሔረ ሰብ” ሲባል ፥ ወይስ “ሕዝቦች” ሲባል?

ከዚያም አልፈው ፥ ሰፍረን የተገኘንበትን ቦታ ለሁላችንም ሳይሰጡን ፥ “ለሁላችሁም ሰጥተናችኋል” ብለው ፥ ትንሾችን የትልቆች ሰለባ አደረጓቸው ። ብዙዎቻችንን የአማራ ፥ የትግራይ ፥ የኦሮሞዎች ጥገኞች አደረጉን ። ይህ መፍትሔ እሌላ አገሮች ተሞክሮ አልሠራም ፤ እዚህም ሳይሠራ እያየነው ነው ። የሕዝብ አገልጋዮች በሚሾምበት ጊዜም ሥልጣንንን በጎሳ ማከፋፈል ሊመጣ ነው ። እርግጥ ፥ የክልልን ሥርዓት የወደዱት አሉ ፤ እነሱ በውስጣቸው የሚኖሩ አናሳ ጎሳዎች መብት ቢጣስ ባይጣስ ግድ የሌላቸው ትልቆች ግን ኋላ-ቀር ነገዶች ናቸው ።

የአንድ አገር ሕዝቦች ሆነን መኖር በግድም በውድም ከወሰንን ፥ የአንድ ሀገር ሕዝብ የሚያደርጉንን ምክንያቶች ፈልገን መኮትኮት ይኖርብናል ። አለባብሰን አንረስ ፤ እንደማየው ፥ “በባህል በዘር አንድ ነን” ማለቱ ብቻውን አላዋጣንም ። ምክንያቱም ፥ በባህል በዘር አንድ አይደለንም ። በባህል ረገድ ሱማሌዎች ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ይልቅ ለነዚያዎቹ ሱማሌዎች ይቀርባሉ ። ጉሙዞችና ጋምቤላዎች ከትግሬዎች ይልቅ ለደቡብ ሱዳኖች የበለጠ ይቀርባሉ ። ከዓሥር ዓመት ግድም በፊት ዋሺንግቶን ዲሲ ስብሰባ አድርገን ነበር ። ከተናጋሪዎቹ አንዱ ጥቁር አሜሪካዊ በከተማው አስተዳደር ውስጥ ባለሥልጣን ነበር ። “እንኳን ደኅና መጣችሁ” ካለ በኋላ ፥ “እኛ እንቀበላችኋለን ፤ እናንተ ግን አትቀበሉንም” አለን ። እኔም ደርሶብኛል ፤ አንድ ስብሰባ ላይ ጸሐፊያችን አፍሪካዊት ነበረች ፤ ላይቤሪያዊት ትመስለኛለች ። ሁሉን ስታነጋግር እኔን ትሸሸኝ ነበር ። ሲያጋጥመኝ ፥ “ብታነጋግሪኝ ቁንጅናሽን እንዳልነካብሽ ቃል ልግባልሽ” ብላት ፥ “ደግሞ እናንተ ኢትዮጵያውያን ከመቼ ወዲህ ነው በጥቁር ሰው ላይ ቁንጂና የምታዩት?” አለችኝ ። “አየሃት ያቺን ልጅ? ልክ አበሻ/ኢትዮጵያዊት ትመስላለች” እንላለን ። የትኛዋን ኢትዮጵያዊት ነው የምትመስለው? ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም አንዲት ኤርትራዊት ለማግባት ቢፈልጉ ፥ ኦሮሞ ስለሆኑ ፥ ዘመዶቿ እንደከለከሏቸው እትዝታ መጽሐፋቸው ውስጥ መዝግበውታል ።

በአንድ ሕዝብነት አብሮ መኖር ግዴታችን ሆኗል ። ግዴታችን ከሆነ ፥ ግዴታችንን በሰላም የምንወጣውና በደስታ የምንኖረው ስንከባበርና አንዱ የሌላውን ችግር ሲገነዘብ ፥ ተገንዝቦም አብሮ በሰላም እንዳንኖር ላደረገን ችግር አብረን መፍትሔ ስንፈልግ ብቻ ነው ። እንደመናቅ (“ና” ትጠብቃለች) የሚያስቆጣ ነገር የለም ፤ ከልጆች መሰዳደብ ሲያልፍ ክብር ይነካል ። መናቅ እንኳን ሕዝብን አንድን ሰውም ቢሆን ሊታገሡት የማይገባ ጠባይ ነው ። ወያኔዎችን ከምንጠላበት ምክንያቶች አንዱ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ዎች ሊያደርጉን ሲሞክሩ በማየታችን እንደሆነ አንረሳም ። ንቀት ኃጢአት ነው ፤ እግዚአብሔርን ያስቆጣል ። ክርስቲያን የሆነ ሌላውን ከናቀ ንስሐ መግባት አለበት ። “ወንድሙን ደንቆሮ የሚል ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል” ይላል ቅዱሱ መጽሐፍ ። ሌላውን የሚንቅ ራሱን የናቀ የሰላም ጠላት ርኩስ ሰው ነው ።

ካህናት መገናኛ ብዙኃን ፊት ቀርበው እንዲህ ያሉ ሰዎችን ሲገዝቱ መስማት እንፈልጋለን ። ሆኖም ፥ አንዱ በናቀ በነገዱ መቀየም ስሕተት ነው ። አሜሪካን አገር ለጥቁሮች መከበር ብዙ ነጮች መሥዋዕት ሆነዋል ።

ከላይ እንዳልኩት ፥ የአንድ አገር ሕዝቦች ሆነን መኖርን አምላክ ከወሰነልንና እኛም ውሳኔውን ከተቀበልን ፥ አንድ ሕዝብ የማያደርጉን ምክንያቶች የሚወገዱ ከሆኑ መወገድ ፥ የማይወገዱ አመሎች ከሆኑ በጉያችን መያዝ ፥ አንድ የሚያደርጉንን ምክንያቶች ፈልገን መኮትኮትና ማዳበር ይኖርብናል ። ሥልጡን ሕዝብን ከኋሊ-ቀር ሕዝብ የሚለየው ይህ ተግባር ነው ። የአሜሪካን መንግሥት የተለያዩ ሕዝቦቿን በአንድ ሕዝብነት ለማስተዳደር የሚያሳየውን ጥረት እንመልከት ። ጥረቱ ልጆች ከሚያድጉበት ትምህርት ቤት ይጀምራል ።

ደግነቱ ፥ እኛንም የአንድ ሀገር ሕዝብ የሚያደርጉን ብዙ ምክንያቶች አሉን ። የተፈጥሮ መኖሪያችን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ከሆነ ሁላችንም እኩል ኢትዮጵያውያን ነን ። የጋራ ሀገር አንድ ሕዝብ ስለሚያደርግ ፥ ኢትዮጵያዊነት አንድ ሕዝብ ያደርገናል ። የሌላ አገር ዜጋ ካልሆነ ፥ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ሊል አይችልም ። ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ካለ ደግሞ ፥ አገሬ ነው ወደሚለው አገር መሄድ ወይም በሀገር-አልባነት መመዝገብ ይኖርበታል ። ሌላ ሰላማዊ አማራጭ የለውም ።

ሰዎችን አንድ ሕዝብ የሚያደርገው ሌላ ምክንያት ታሪክ ነው ። የዚህ ምክንያት ባለጸጎች ነን ። የውጪ ወረራን የነገዶች አባቶቻችን አብረው መክተዋል ። በዘመነ መሳፍንት ወድቃ የነበረችውን ኢትዮጵያን የነገዶች አባቶቻችን አብረው አንሥተዋታል ።

ሌላው የአንድነታችን ምልክት አንድ አገራዊ ቋንቋ (አማርኛ) በሁሉ ቦታ መታወቁ ነው ። የመስፋፋቱን ታሪክ ትኩር ብለን ስንመለከት በዘመን ብዛት ቋንቋው ወደ ጎሳዎች ፥ ጎሳዎች ወደ ቋንቋው መጥተው እንደተገናኙ እናያለን ። ውጤቱ ሁለት ዓይነት ሆኗል ፤ ቋንቋውና ቋንቋውን የማያውቁ ጎሳዎች በመገናኘታቸው ምክንያት የተገናኙትን ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ያደረጉ ሰዎች ወይ አማራ ሆነዋል ወይም የጥንት ጎሳቸው አባላትነት ይሰማቸዋል ። አማራ የሆኑት የአማራውን ቍጥር አብዝተውታል ። ዛሬ "አማርኛ ተናጋሪ እንጂ ፥ አማራ የሚባል ዘር የለም" የሚባለው ስለዚህ ነው ። ሌሎቹ የጎሳ ቋንቋቸውን ባያውቁም ፥ የዚያ ጎሳ ሰዎች መሆንን ይመርጣሉ ። አሜሪካን አገር እንግሊዝኛ ብቻ እየተናገሩ ፥ "አየሪሽ ነኝ" ፤ "ጀርማን ነኝ" ፤ "ጣልያን ነኝ" እንደሚሉት አሜሪካኖች ማለት ነው ። ቋንቋ መነጋገሪያ መግባቢያ ስለሆነ ፥ በማንኛውም ቋንቋ ቢጠቀሙ ከመግባቢያነቱ ያለፈ ዋጋ የማይሰጡ ኢትዮጵያውያንም አሉ ።

ታላቁ የምሥራች ፥ ሁሉን እኩል በሚያደርገው በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር (በዳምጠው) የማይምል ፖለቲከኛ ኢትዮጵያዊ አላጋጠመኝም ። ዲሞክራሲን ሁላችንም ከሚያስከትለው ነፃነትና ግዴታ ጋር ተቀብለነዋል ። ዲሞክራሲ ምድራዊ ሃይማኖታችን መሆኑን ከተቀበልን ፥ ቅዱስ መጽሐፋችን አብረን የምናረቀው ሕገ መንግሥት ይሆናል ። እዚያ ላይ እናትኩር ። ዲሞክራሲ ሥር የሚሰድበትን ማሳ እናለስልስ ። የሚቆምባቸው ተቋማት እስኪቋቋሙ አንተኛ ፥ አናንቀላፋ ። ዶክተር ዐቢይ የሚቀጥለው ምርጫ ማጭበርበር የሌለበት ይሆናል ብሎናል ፤ አምነዋለሁ ።